# በባሕር ዳሩ የኢሕአዴግ ስብሰባ በአመራሮች ሹም ሽር ይካሄዳል

## የEMF ዘጋቢ ከአዲስ አበባ - 24 January 2010

በአቶ መለስ ዜናዊ የተመራ የኢህአዴግ ሥራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ባልተለመደ ሁኔታ ከአዲስ አበባ ውጪ በባህር ዳር ከተማ የአማራ ክልል መስተዳድር ፅ/ቤት ውስጥ ከረቡዕ ጥር 12/2002 ምሽት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ንደሚገኝ ከታማኝ የዜና ምንጮቻችን ያገኘ ነው ዜና ያስረዳል::

ከአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች ሕወሓት፣ ብአዴን፣ ኦሕዴድና ደኢሕዴን የተውጣጡ የኢሕአዴግ ሥራ አስፈፅሚና ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በተጨማሪ አዳዲስ ፊቶች የታዩበት ስብሰባ በሚቀጥለው ዕሁድ ሲጠናቀቅ በርካታ የግንባሩ አመራሮች ከድርጅት ሃላፊነታቸው እንደሚባረሩና በአቶ መለስ ዘናዊ ታማኝ «ወጣቶች» እንደሚተኩ በካድሬዎች አማካይነት የተገለፀ መሆኑንም ውስጥ አዋቂ ምንጮቻችን ገልፀዋል::

በሌሊት እየተካሄደ የሚገኘውና መለስ ዜናዊ የሚመሩት የባህር ዳሩ ስብሰባ ሲጠናቀቅ በማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላ ጉባኤው ከየድርጅቱ የሚሠየሙ በርካታ አባላት ጭምር እንደሚቀየሩ ታውቋል፤ በዚሁ መሠረት 80 አባላት ከሚገኙበት ከአራቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች ከ ያንዳንዳቸው ሃያ አባላት ለጠቅላላ ጉባኤው የሚሠየሙ ሲሆን ብአዴንና ኦህዴድ ግማሽ ያህል አባላቸውን እንደሚቀይሩ ሲገለፅ፣ ህወሐትና ደኢህዴን አራት አራት አባላት ብቻ እንዲለውጡ ይደረጋል::

«ኢሕአዴግ አዳዲስ አመራሮችን በወጣቶች ተካለሁ» የሚል ሃሣብ ይዞ መምጣቱን ቢናገርም የስብሰባው ዓላማ ግን መለስ ዜናዊ አመራር አልተመቹም የተባሉ የብአዴንና ኦህዴድ ተሿሚዎችን ከወንበራቸው ለማንሳት የተደረገ «ዘመቻ» መሆኑን የሚገልፁት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የተሠናባች አስተዳዳሪዎች ማንነት ከእሁዱ ግምገማ ማጠቃለያ በኋላ እንደሚገለፅ የተነገራቸው መሆኑን ጠቁመዋል:: ባለሥልጣናቱ የቀረበባቸው የአቅምና ብቃት ማነስ የሚል ክስ ቢሆንም በተለይ ብአዴን ውስጥ ያሉ አመራሮች ለ መለስ አለመመቸታቸው የተጠቀሰ ሲሆን፣ በምትካቸው የሚሾሙት «ወጣት» ካድሬዎችም የመለስን ትዕዛዝ ያለ አንዳች ጥያቄ ተቀብለው ሥራ ላይ የሚያወሉ መሆናቸው ሣይታለም የተፈታ ነው» ብለዋል::

በዚሁ መሠረት ከብአዴን በጭንቅላት ቲዩመር የሚሠቃዩትና ወደ ደቡብ አፍሪከ ለህክምና የሚመላለሱት አቶ በረከት ስምኦን፣ አቶ ተፈራ ዋልዋና ቀደም ሲል የግብርና ሚኒስትርነታቸውን የተነጠቁት አዲሱ ለገሠ ቦታቸውን ለወጣቶች እንደሚያስረክቡ የተገለፀ መሆኑን የጠቀሱት ምንጮቻችን ከኦህዴድ ሽፈራው ጃርሶ፣ ጁነዲን ሣዶና ሙክታር ከድርን ጨምሮ በፓርቲው አመራር ላይ የሚገኙ በርካታዎች እንደሚሠናበቱ ለተሠብሳቢዎች በካድሬዎች አማካይነት የተገለፀ መሆኑን ምንጮቻችን ጠቅሰዋል::

ከተሰናባች ኢሕአዴጋውያን የተወሰኑት ብቻ «የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ» በሚል ሽፋን እንዲቆዩ የሚደረግ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ ኢሕአዴግ ይሕን ስልት በውስጣችን መከፋፈል የለም ለማስባል በተደጋጋሚ የሚሰራበት መሆኑም የተወቀ ነው:: ኢህአዴግ በሚቀጥለው ሣምንት በፓርቲው ልሣን «ሕዳሴ» አማካይነት አዳዲስ የማዕከላዊ

አባላቱንና የምርጫ ተወዳዳሪዎቹን ይፋ እንደሚያደርግም ውስጥ አዋቂዎች ይፋ አድርገዋል።

# የመለስ ዜናዊ ቢሮ ሃላፊ ላይ መፈንቅለ ሥልጣን ተሞከረ

**የEMF ዘጋቢ ከአዲስ አበባ**

የመለስ ዜናዊ ቢሮ ሃላፊ በሆኑት አቶ ብርሃኑ አዴሎን በ«መፈንቅለ ሥልጣን» ለማባረር አቶ በረከት ስምኦንና አቶ ሃይለማርያም ደሳለኝ የተቀነባበረ ሴራ በማካሄድ ላይ እንደሚገኙ ተጠቆመ። ይህን ዘመቻ እንዲመሩ ሳፊነቱን የተረከቡት የቀድሞው የኢትዮጵያ ፉትቦል ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ ሲሆኑ፣ ግለሰቡ ዓላማውን ለማሣካት የሚያስችላቸውን ጋዜጣ ፈቃድ ያወጡ ሲሆን ከሚቀጥለው ሣምንት ጀምሮ ጋዜጣውን ማሳተም እንደሚጀምሩም ታውቋል።

የመለስ ዜናዊ ቢሮ ሃላፊ የሆኑትን አቶ ብርሃኑ አዴሎ ከከፋ አካባቢ ኢህአዴግን ወክለው የመጡ ሲሆን፣ በሁለቱ የኢህአዴግ አመራሮች በአቶ በረከትና በአቶ ሃይለማርየም ደሳለኝ ጥርስ የተነከሰባቸው በመሆኑ በአካባቢያቸው ህዝብ የመተማመኛ ድምፅ አጥተዋል የሚል ቅስቀሳ ተደርጎባቸው እንዲነሡና ዘርፈዋል በሚባለው የሚሊየን ብሮች ሙስና በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን ምንጮቻችን ያስረዳሉ።

ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ ባለፈው ዓመት በተካሄደ የማሟያ ምርጫ በግል ተወዳድረው ሣይሣካላቸው መቅረቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ከአራት ወር በኋላ ግን በትውልድ መንደራቸው ቦንጋ ኢህአዴግን ወክለው ለመወዳደር መዘጋጀታቸውን ታማኝ የዜና ምንጮች ገልፀዋል። ከምርጫው በኋላ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ሃላፊነት ወንበርን እንደሚያገኙ በእነ በረከት ስምኦን ቃል የተገባላቸው የጥርስ ሃኪሙ አሸብር የአሁኑን ሃላፊ በሙስና ለማሣሠር ራሳቸው በተውኔቱ የተሳተፉ ሲሆን፣ ለዚሁ አገልግሎት ተብሎ የሚዘጋጀውና ባለፈው ሳምንት ከማስ ታ ወቂያ ሚኒስቴር ሂደቱ የተጠናቀቀለት ጋዜጣ በሚቀጥለው ሣምንት ውስጥ ታትሞ እንደሚወጣም ታውቋል።

ዶክተር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ በምርጫ 97 ወቅት መኪናቸውን ወደ ደቡብ ክልል በመላክ ለኢህአዴግ ቅስቀሳ ያደርጉ በነበረበት ወቅት ከነፃ ጋዜጠኞች ትችት ሲቀርብባቸው «...ፈፅሞ ፖለቲካ ውስጥ የለሁበትም» ሲሉ ቢከርሙም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን በተደጋጋሚ በደኢህዴን ስብሰባዎቹ ፊት ወንበር ላይ ተቀምጠው በቴሌቪዥን መስኮት እየታዩ ይገኛሉ።

# ኢዴፓና ኢህአዴግ የምርጫ ቦታ ስብስብ ያደርጋሉ

**የEMF ዘጋቢ ከአዲስ አበባ**

በምርጫ 2002 የሚሳተፉ የኢህአዴግ አባላት ካለፈው ሠኞ ጥቅምት 11/2002 ዓ.ም ጀምሮ ለአንድ ሣምንት በአዳማ ከተማ ጉባኤ በተቀመጡበት ወቅት የኢዴፓ አባላትም አብረው በዚሁ ስብሰባ መሳተፋቸውን የዜና ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

347 የኢህአዴግ ተመራጮች በአዳማ (ናዝሬት) ጨፌ ኦሮሚያ አዳራሽ «የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ» በሚል ርዕስ በተወያዩበት መድረክ ከ60 ያላነሱ የኢዴፓ አባላት መሳተፋቸውን የገለፁልን የዜና ምንጮቻችን ለመገናኛ ብዙሃን ክፍት ባልነበረው መድረክ ኢህአዴግና ኢዴፓ በምርጫ ሥነ-ደንቡ ላይ የደረሱበት መግባባት በአንዳንድ ቦታዎች የምርጫ ቦታ ሽግሽግ ስከማድረግ ንደሚደርሱ በይፋ መነገሩም ተጠቁሟል፡፡ በዚሁ መሠረት በሁለቱ ድርጅቶች አመራሮች በሚደረግ ድርድር ከከተማ ርቀው በሚገኙ በሚገኙ የምርጫ መወዳደሪያ ቦታዎች በተወሰኑት የኢዴፓ አባላት እንዲመረጡ ሲባል ኢህአዴግ ተወዳዳሪዎቹን ስከማንሣት ሊሄድ እንደሚችልም ተገልጿል፡፡ ኢዴፓ በታማኝ ተቃዋሚነቱ የተወሰነ ወንበር ይዞ ንዲቀጥል ሲባል ርምጃው መወሰዱን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡

በልደቱ አያሌው የሚመራው ኢዴፓ፣ በኢንጅነር ሃይሉ ሻውል የሚመራው መኢአድና ኢህአዴግ በሦስትዮሽ የተስማሙበት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሠኞ ጥር 17/2002 ሥራውን ይጀምራል የተባለ ሲሆን፣ ይሕ አካል ከምርጫ ቦርድ የተለየ ምንም ሚና እንደሚኖረው ግን ብዙዎችን ግራ አጋብቷል፡፡

# መድረክ በመስቀል አደባባይ ለሚጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ ፍቃድ ተከለከለ

**የEMF ዘጋቢ ከአዲስ አበባ**

ኢሕአዴግና ጋሻ ጃግሬዎቹ ባዘጋጁት የ«ፓርቲዎች ስነምግባር ደንብ» ላይ ለመወያየትና ለመደራደር የሁለትዮሽ ድርድር ብቻ ያስፈልጋል ያለው የስምንት ፓርቲዎች ስብስብ የሆነው *መድረክ ለዲሞክራሲያይዊ ትብብር በኢትዮጵያ* (*መድረክ*) «ህዝባዊ ስብሰባን በአዲስ አበባ ለማድረግ በተደጋጋሚ ጥያቄ አቅርበን ከብዙ መጉላላት በኋላ በአዲስ አበባ የመሰብሰቢያ ማዕከል አንድ ሺሕ አንድ መቶ ሰው በላይ መሰብሰብ አይችሉም የሚል መመሪያ ንደደረሳቸው» ገልፀው የነበረ ሲሆን፣ የመድረኩ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊዎች ለአዲስ አበባ መስተዳድር ጽ/ቤት ደንቡና መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት በመስቀል አደባባይ ለመሰብሰብ ጥያቄ አቅርበው መከልከላቸው ውቋል፡፡ መስተዳድሩ መድረክ ላቀረበው ጥያቄ «ቦታው (መስቀል አደባባይ) ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የማይፈቀድለት መሆኑ የታወቀ እንዲሕ ያለ ጥያቄ መቅረቡ አግባብ አይደለም» የሚል ነው፡፡ የመድረኩ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊዎች ይህ መሰሉ ርምጃ የሚወሰድባቸው ከደጋፊዎቻቸው ጋር በስፋት ንዳይገናኙ ሆን ተብሎ የሚፈፀም ደባ መሆኑን ነው የሚያምኑት፡፡ መስቀል አደባባይም እስከ ምርጫ 97 የበርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሰባሰቢያ መድረክ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል፡፡